የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፴፪
አዲስ አበባ ሰኔ ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፫

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

7th Year No. 32
ADDIS ABABA - 28th June, 2001


## ማውጫ


አዋጅ ቁጥር ፪፻፵፬/፲፱፻፺፫ ዓ·ም·
ለደምቢ–በደሌ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት የተገኘው ብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ..................................... ገጽ ፩ሺ፭፻፴፪


## CONTENTS


Proclamation No. 244/2001
Arab Bank for Economic Development in Africa Loan Agreement for Financing the Dembi-Bedele Road Project Ratification Proclamation .. Page 1532


### አዋጅ ቁጥር ፪፻፵፬/፲፱፻፺፫

### በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለደምቢ–በደሌ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ፱ ሚሊዮን ፪ መቶ ሺ የአሜሪካን ዶላር (ዘጠኝ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሺህ የአሜሪካን ዶላር) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት መካከል እ·ኤ·አ· ፌብሩዋሪ ፳፪ ቀን ፪ሺ፩ በካይሮ የተፈረመ በመሆኑ፤

መሠረታዊ የኢኮኖሚ ዓለም አቀፍ ውሎች ተፈፃሚ ከመሆናቸው በፊት መፅደቅ ስላለባቸው፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ·ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፤

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ (፩) እና(፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለደምቢ–በደሌ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት የተገኘው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፪፻፵፬/፲፱፻፺፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

*PROCLAMATION No. 244/2001*
*A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE ARAB BANK FOR ECONOMIC DEVELOPMENT IN AFRICA*

WHEREAS, a Loan Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Arab Bank for Economic Development in Africa stipulating that the Arab Bank for Economic Development in Africa provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan amount of USD 9,200,000 (nine million two hundred thousand United States Dollars) for financing the Dembi– Bedele Road Project was signed in Cairo, on the 22nd day of February, 2001;

WHEREAS, basic economic international agreements have to be ratified prior to entry into force;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 28th day of June, 2001;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Arab Bank for Economic Development in Africa Loan Agreement for Financing the Dembi-Bedele Road Project Ratification Proclamation No. 244/2001."


ያንዱ ዋጋ 2·30
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

## ፪· ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ "የብድር ስምምነት" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት መካከል እ·ኤ·አ· ፌብሩዋሪ ፳፪ ቀን ፪ሺ.፩ በካይሮ የተፈረመው የብድር ስምምነት ነው።

## ፫· የገንዘብ ሚኒስትሩ ሥልጣን

የገንዘብ ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘው ፱ ሚሊዮን ፪ መቶ ሺ የአሜሪካን ዶላር (ዘጠኝ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሺ የአሜሪካን ዶላር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

## ፬· አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከሰኔ ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ·ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሰኔ ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ·ም

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት



## 2. *Definition*

In this Proclamation "Loan Agreement" means the Loan Agreement signed in Cairo, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Arab Bank for Economic Development in Africa, on the 22nd day of February, 2001.

## 3. *Power of the Minister of Finance*

The Minister of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the loan amount of USD 9,200,000 (nine million two hundred thousand United States Dollars) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

## 4. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 28th day of June, 2001.

Done at Addis Ababa, this 28th day of June, 2001.

NEGASO GIDADA (DR.)

PRESIDENT OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE